

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከሜይ 21-31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ እንዲሁም

## ከጁን 1-10 እና ከጁን 11-20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

## እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2025

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ አና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 16.7፣ በአርባምንጭ 17.8፣ 48.8፣ ባህር ዳር 49.2፣ ደብረ ማርቆስ 30.2፣ ጎንደር 16.4፣ 16.2፣ ጎሬ 25.8፣ 24.7፣ ጅማ 31.2፣ 19.8፣ ነቀምት 62.5፣ 17.2፣ 19.3፣ አቦቦ 48.4፣ አይራ 20.5፣ 37.5፣ 23.8፣ 36.8፣ አማኑ 17፣ 43፣ 16.7፣ 52.1፣ 16.3፣ አንገር ጉቲን 25.4፣ 52.4፣ 52.4፣ አርጆ 22.4፣ 28.2፣ 16.6፣ 18.6፣ አሶሳ 25.5፣ 31.3፣ አየሁ 40፣ 15.5፣ 23.5፣ አይከል 53.7፣ 36.4፣ በደሌ 32.3፣ 37.8፣ ቦሬ 17.4፣ 22.6፣ 21.5፣ ቡለን 22፣ ቡሬ 19.6፣ 23.5፣ ቻግኒ 32.7፣ 17.6፣ ጨዋቃ 25.5፣ 35፣ ጭራ 23፣ 19.9፣ 38.4፣ 19.9፣ ዳንግላ 38.3፣ 46፣ ደባርቅ 23፣ 34.1፣ 22.4፣ ደበረ ተቦር 15.9፣ ደብረ ወርቅ 15.2፣ ዲላ 37.5፣ 18.2፣ ኢጃጂ 23.5፣ 19.4 ፊቼ 19.6፣ ፉኙዶ 34፣ ጋምቤላ 36.2፣ ጋቲራ 40.6፣ 22.6፣ 26.1፣ 33.8፣ 30.2፣ 28.4፣ 16.4፣ ወሊሶ 28.9፣ 23.5፣ ጊዳ አያና 24.4፣ 28.8፣ 41.2፣ 22.6፣ ጊምቢ 18.9፣ 38.1፣ ጉንዶ መስቀል 19.8፣ ቡሌ ሆራ 16.8፣ 22.5፣ ሆሳዕና 25.7፣ 24.1፣ እምድብር 21.2፣ 23.6፣ ጂንካ 81.3፣ ኮንሶ 17.5፣ ላይ ብር 29.8፣ ሊሙ ገነት 22.9፣ 26.4፣ ነጆ 37.5፣ 21.8፣ 24.6፣ ሰዉላ 28.6፣ 21.8፣ ሶከሩ 19.7፣ ሻዉራ 56፣ 19.6፣ ሻምቡ 16፣ 27.4፣ ቴፒ 28.9፣ 47.7፣ 57.2፣ ወራቤ 22.2፣ 17.4፣ 15 እንዲሁም ወላይታ ሶዶ 30.1 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ29 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-81.3 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ጂንካ፣ ነቀምት፣ ቴፒ፣




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሻዉራ፣አይከል፣ አንገር ጉቲን፣ አማን፣ በህርዳር፣ አርባምንጭ፣ አቦቦ፣ ዳንግላ፣ ጊዳ አያና፣ ጋቲራ፣ አየሁ (ምስል 1)፡፡




ምስል፡1 ከሜይ 21-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ኮሬ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ፣ አሪ፣ ጋርዱላ ዞኖች ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ የሰሜን፣ የምዕራብ፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ አዊ፣ የሰሜን ሸዋ እና ዋግህምራ ዞኖች፣ ከትግራ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ21-220 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ኮሬ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ፣ አሪ፣ ጋርዱላ ዞኖች ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ የሰሜን፣ የምዕራብ፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ አዊ፣ የሰሜን ሸዋ እና ዋግህምራ ዞኖች፣ ከትግራ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ዞኖች፣ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር


በሌላ በኩል በሰመራ፣ በገዋኔ፣ በመተማ፣ በአይሻ፣ በአዋሽ አርባ፣ በመተሃራ፣ ጭፍራ፣ በፉኙዱ፣ በድሬ ዳዋ፣ በጋምቤላ፣ዲሊፋጊ፣ መካነ ሰላም፣ ሸዋሮቢት፣ ጎዴ፣ በጨፋ፣ በአቦቦ፣ በመኢሶ፣ በቀብሪዳሀር፣ ኑራ ኤራ፣ ማጀቴ፣ በጨዋቃ፣ ላይብር፣ በባቲ፣ በቻግኒ፣ በምዕራብ አባያ፣ በሻምቡ፣ በቴፒ፣ በአሶሳ፣ ጎንደር፣ አይደር፣ ጅግጅጋ፣ ኮምቦልቻ፣ አቦምሳ፣ ወግል ቴና፣ አየሁ፣ በብላቴ፣ በህርዳር፣ አይራ፣ሓሮማያ፣ ቡሂ፣ ጊምቢ፣ አዳሚ፣ ሰዉላ፣ እና ሲርንቃ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 33.0 እስከ 46.2 ዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት የሜይ የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከእርጥበታማ (moist) እስከ በጣም እርጥበታማ (Humid) ሁኔታ ስር እንደነበሩ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ሁኔታ ዕድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከኤፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ እንደ ቦቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እድገት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፣ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ከባድ ዝናብ ምንም እንኳን በጥቂት ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ቢኖረውም ለአብዛኛው የእርሻ እንቅስቃሴ ጠቀሜታው የጎላ ነበር፡፡ በሌላ በኩል በብዙ የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት አስቀድመው የማሳ ዝግጅት እንዲያከናውኑና በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበርዉ (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሜይ ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ተከዜ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ እንዲሁም መረብጋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ ይህንም ሁኔታ ለከርሰ ምድር ሆነ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መጎልበት አውንታዊ ጎን እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን እና አይሻ ተፋሰሶች በደረቅ የእርጥበት ሁኔታስር ነበሩ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ ወቅታዊው የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል:: በጁን በመደበኛው ሁኔታ የሚታየው የዝናብ መጠንና ስርጭት የተሻለ መልክ የሚኖረው ከወሩ ከመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ጀምሮ ነው። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ15-24 ቀናት ያህል ይዘንባል። ይሁንና በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ30-100ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ3-16 ቀናት ያህል ይዘንባል። ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁን የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ 30% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

### 2.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁን የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)። ከዚሁ ጋር በተያያዘም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

### 2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች በተጨማሪ የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ቦረና፣ አርሲ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| አማራ | የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ዞኖች የደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና የመካከለኛዉ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ፋፈን፣ ሲቲ፣ ኤረር፣ ጃራር፣ ዶሎ፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በጁን የመጀመሪያው አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በአፋር ክልልና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሊይ ከ30 እስከ 35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 7)፡፡





ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.3 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁን ሁለተኛዉ አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ሳምንት ነው፡፡

በመጪዎቹ የጁን ሁለተኛዉ አሥራ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄድ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከጁን 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.4 እ.አ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ለወቅቱ የእርሻ ስራ እንቅሥቃሴ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

በአጠቃላይ በመጪው የጁን የመጀመሪያዉ አስር ቀናት የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም ከታች የተሰጡትን የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ የሰሜን፣ የምስራቅ እና የምዕራብ ጎጃም፣ የደቡብ ጎንደር፣ አዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን<br>• ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገትና የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል<br>• ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት | • የእርጥበት መብዛትን በማይቋቋሙ የአፈር ጠባይ ያላቸው ማሳዎች መጨቅየት እና የውኃ መተኛት<br>• ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር እርሻን ቀድመው ለመጀመር የማሳ ዝግጅት ማከናወን እና ዘር መዝራት<br>• የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋል።<br>• |
| ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ቦረና፣ አርሲ፣ የሰሜን እና የመካከለኛዉ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን<br>• ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል<br>• ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት | • ከፍተኛ ትነት በሚኖርባቸዉ አካባቢዎች መጠነኛ የሆነ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መኖር | • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን<br>• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |
| **የመኸር አብቃይና በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑ ዞኖች** | | | | |



ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የደቡብ ትግራይ ዞኖች ፣ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ኤረር፣ ጃራር፣ ፋፈን እና ሲቲ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛመ ጠንያለዉ እርጥበት | • ለበልግ ሰብሎች እድገት<br>• ለመኸር ግብርና እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• ከፍተኛ ትነት መኖር | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር የማሳ ዝግጅትና የዘር መዝራት ማከናወን<br>• የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን<br>• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፤ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች እና ሁሉም የሲዳማ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገትና ፍሬ ለማፍራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት<br>• የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | • ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር | • ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብሎች ላይ መተኛትን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ይህንን ለመከላከል የሚያስችሉ የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራትና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በማዘጋጀት የቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራት<br>• የአፈርና የውሃ እቀባና የእርከን ስራ ማከናወን |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ ዶሎ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለተዘሩ ሰብሎች እድገትና ፍሬ ለማፍራት<br>• የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• የሚኖረው እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | • የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |

## 2.5 ኢ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት የጁን የመጀመሪያ አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና የሚገኙ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኛሉ። ይህ ሁኔታ የገጸ ምድር እንዲሁም ከረሰ ምድር ዉሃ ውኃ ሀብት መጠን መጨመር አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ እርጥበት አጠር በሆኑ ሆኑ ተፋሰሶች የተለያዩ የዉሃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ዉሃን ማጠራቀም አስፈላጊ ነው፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ተፋሰሶች | የሚጠበቀው እርጥበት | አዎንታዊ ተፅዕኖ | አሉታዊ ተፅዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣በላይኛው እና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ታችኛው አባይ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመስኖ እና የሀይል ማመንጫ ግድቦች የውኃ ክምችት መሻሻል<br>• ወኃ አቅርቦት መሻሻል | •<br>• የውሃ በጎርፍ መበከል<br>• የቅጽበታዊ ጎርፍ ክስተት<br>• | • የጎርፍ መፋሰሻ ቦዮችን ማጽዳት<br>• የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም<br>• በወንዝ ዳርቻ የሚኖሩ ግንዛቤ መስጠት ወይም ማስጠንቀቅ<br>• ትንበያዎችን በቅርበት በመከታተ<br>• የጎርፍ ውኃን ማሰባሰብና ማከማቸት |
| በአብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ በላይኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ | ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• | •ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውኃ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ማሰባሰብ እና ማጠራቀም<br>• የሚገኘውን የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር<br>• የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከመሬት እና ጣራ ላይ የዝናብ ውኃ የማሰባባሰብ ተግባራትን ማከናወን |
| በአብዛኛው በአይሻ፣አፋር፣ደናከል፣መረብ.ጋሽ፣አዋሽ፣ ተፋሰሶች | ደረቅ ሁኔታ | • ወራጅ ዉሃ በተለያዩ ፍሳሽ አለ መበከል<br>• ወደ ውኀ ማጠራቀምያዎች የሚገባ ደለል መቀነስ | •የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀምያዎች የዉሃ መጠን መቀነስ<br>•በቂ ውሃ አለ መኖር | • ዉሃን በአግባቡ መጠቀም<br>• ዉሃን አክሞ መጠቀም በተለይ የታቆሩ እና የጉድጓድ ዉሃ |

Ethiopian Meteorology Institute



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et